የመልአልተ አድባራት ቀራንዮ መድኃኔዓለምና ቅዱስ ገብርኤል

አብያተ ክርስቲያናት

አንቀጸ ተዋሕዶ ሰ/ት/ቤት

የጸሎተ ዓርብ መመሪያ

አዘጋጅ ፦ የሰ/ት/ቤቱ ጉባዔ አደራጅ ክፍል

የካቲት 03/2015 ዓ.ም.

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልአልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

በሰመ አብ ወወልድ ወመንፈሰ ቅዱሰ አሐዱ አምላክ አሜን።

ጸሎት ማለት፦ጸለየ፣ለመነ፣ ጠየቀ አማለደ፣ ማለደ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ቃል ነው። ጸሎት ማለት ጠቅለል አድርገን ሰንመለከተው ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እግዚአብሔርን ማመሰገን መለመን፣ መጠየቅ፣ መማለድ፣ መማፀን ነው። “ጸሎትሰ ይእቲ ተናግሮተ ሰብእ ኀበ እግዚአብሔር ልዑል።/ ጸሎትሰ ሰው ከልዑል እግዚአብሔር ጋር የሚነጋገራት ነገር ናት።" እንዲል። ፍት.ነገ 14 ÷ 5 28 አባታችን አዳምም ከመላእክት ተምሮ በየሰዓቱ ይጸልይ ያመሰግን ነበር ። ዲያብሎስ በእባብ አድሮ ወደ አዳም በመጣ ጊዜ ጸሎት እያደረገ ሰለነበር ዲያብሎስን ድል ነሥቶታል ሔዋንን ግን ሥራ ፈትታ እግሯን ዘርግታ ሰለአገኛት ድል ነሰቷታል።

ጸሎት ሰማዕታት ከነደደ እሳት፣ ከተሳለ ሰለት፣ ከአላውያን መኳንንት፣ ከአሕዛብ ነገሥታት ከዲያብሎስ ተንኮል እና ሸንገላ ፣ ዲያብሎስ በእነርሱ ላይ ከአጠመደው አሽከላ የዳኑበት ጋሻ ነው። (ኤፌ 6፥10 - 21) ጸሎት ሰው አሳቡን በእግዚአብሔር ላይ የሚጥልበት አሳቡን ለእግዚአብሔር የሚገልጥበት እግዚአብሔርም የሰውን ልመና ተቀብሎ ፈቃዱን የሚፈጽምበት ረቂቅ ምሥጢር ነው። የጸሎት መሠረቱ“ዕሹ ታገኛላችሁ ለምኑ ይሰጣችኋል ደጁ ምቱ ይከፈትላችኋል"የሚለው የጌታችን ትምህርት ነው።/ማቴ7፥7

በጸሎት ጊዜ ለጸሎት የቆመ ማንኛውም አካል የሚከተሉት ክንዋኔዎች መተግበር ይገባዋል

➢ ዓምድ ግድግዳ ሳይዙ በሁለት እግር ቀጥ ብሎ መቆም ይገባል፡ /መዝ5+3/

➢ ፊትን ወደ ምሥራቅ መመለስ ይገባል፡-ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣቱን ተስፋ እያደረግን መጸለይን ያመለክታል።

➢ በመስቀል እምሳል ማማተብ አጋንንትን ድል ለማድረግ/ሉቃ11፥ 20/እንድም ክርስቶስ በመስቀል የከፈለልንን ዋጋ በማሰብ

➢ በመፍራትና በመንቀጥቀጥ የጸሎት ቃላት ማንበብ ይገባል።

➢አስተብርኮ ሰግደት በሚገባ ሰዓት ሰግደት ሊያደርግ ይገባዋል፡ /ማቴ 4+10/ ዮሐ 4፥24/

➢እጆች ማንሣት በጸሎት ሥርዓት ይገባል። /1ኛ ጢሞ 2 ፥ 8, ዮሐ 11፥41/

➢ማንጋጠጥ፡- እግዚአብሔርን መለመን (መማፀንን) ያመለክታል፡ ተስፋ መጠበቅን ምልክት ይሆናል።መዝ123፥1-2

➢ በዜማ መጸለይ፡- በዜማ መጸለያችን በእግዚአብሔር የመደሰታችንን ምሳሌ ነው። ያዕ 5 ፥ 13

➢ አንድ ቃል በመደጋገም መጸለይ ፡- አጽንዖትን ያመለክታል። መዝ 67 ፥ 6 - 7

ጸሎታችን ተቀባይነት እንዲኖረው ማድረግ ያለብን

❖ በመንፈሰ ቅዱሰ እየተመራን መሆን አለበት። ኤፌ 6 ፥ 18

- ልቡናችንን ከዓለማዊ ሐሳብ ከገታን መንፈሰ ቅዱሰ በውሰጣችን ያድራልና።

0903111199 ፣ 0963132564
AnketseTewahido27@gmail.com
መልእልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

❖ በእምነት ሊሆን ይገባል፡

- ሰንጸልይ የምንጠይቀውን ነገር እንደሚደረግልን በፍጹም ልባችን ልናምን ይገባል። ያዕ 1 ፥ 5 - 8

❖ ያለማቋረጥ እና ያለመሰልቸት

- በትጋት ሁልጊዜ ያለመሰልቸት በተሰፋ በመጠበቅ መጸለይ ሉቃ 18 ፥ 1 - 8

❖ በተጋድሎ

- እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ሰንሆን ጥንተ ጠላት በተለያዩ ፈተናዎች እና መከራዎች ይፈትነናል

ሰለዚህ በተጋድሎ (በመጋደል) መጸለይ ኤፌ 6 ፥ 12

❖ ከይቅርታ ጋር

- ቢበድሉ ማሩኝ ቢበደሉ ይቅርታ ማለት ተገቢ ነው። " ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ሰርቆት" እይገባም

መባዕ ለመሰጠት ጸሎት ለመጸለይ ከመሄዳችን በፊት ከሁሉ ጋር በሰላም ልንሆን ይገባል። ማቴ 5 ፥ 23 - 24

❖ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መጠየቅ

- ሰዎች በስሕተት የተሞላን እንደመሆናችን መጠን የምንጠይቀው ነገር ለእኛ የማይጠቅም ሊሆን

ይችላል ሰለዚህም የእነተ ፈቃድ ይሁን ብለን ልንጸልይ ይገባል። ማቴ 6 ፥ 10

የዓርብ ጸሎት – በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን ቅደም ተከተሉ ፦

✥ የዕለቱ መዝሙረ ዳዊት (መዝ 131 -150) ለተማሪዎቹ እንድ እንድ መዝሙር ታድሎ (ተሰጥቶ) በሉኖሳስ በግል ይደገማል። እንደ ተማሪዎቹ ብዛትና በጊዜ መጀመሩ ታይቶ ሙሉ መዝሙረ ዳዊት እና ጸሎተ ነቢያት እንዲሁም መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ሊደገም ይችላል ።

✥ የዘወትር ጸሎት -ውዳሴ ማርያም - ይቄድሰዋ

✥ ጸሎታ ለማርያም በጸሎት መሪው ይደርስና አባታችን ሆይ ይጸለያል

✥ መሐረነ አብ

✥ ጸሎተ ቅዱስ ወንጌል (ምስባክ)

ዋና ጸሎት መሪው በሰመ አብ ብሎ እእትብ እና ነአኩተከን ደግሞ (ብሎ) አቡነ ዘበሰማያትን ያሰደግማቸዋል ፤ ካልሆነም አቡነ ዘበሰማያትን አሰደግሞ ዳዊቱን ይደግማሉ።

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልእልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

ክፍል አንድ መዝሙረ ዳዊት - ውዳሴ ማርያም

የመጀመሪያውን መዝሙረ ዳዊት(መዝ 131) የሚጸልየው ሰው ከመዝሙሩ በፊት የሚለው፦

ነዓ ኀቤየ አምላከ ዳዊት ንጉሠ እስራኤል

ባዕለ መዝሙር ሠናይ ወጥዑመ ቃል

ታለብወኒ ነገረ ወፍካሬ ኩሉ እምሳል

ከመ እወድሳ ለማርያም ድንግል

እንዘ እጸርሕ ወእብል

መዝሙረ ዳዊትሰ ትመሰል ገነተ

እንተ ትጸጊ ጽጌያተ

ወታፈርህ ፍሬያተ

ወታመጽእ በረከተ

ወትስድድ እጋንንተ

ወታቄርብ መላእክተ

ለዓለም ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

ትርጉም ፦

የእስራኤል ንጉሥ የሆነ የዳዊት አምላክ ሆይ ፤ በተወደደ ምሥጋና ሀብትና በተወዳጅ ቃል እንዲሁም በምሳሌያት ሁሉ እመቤቴ ድንግል ማርያምን አመሰግናት ዘንድ ማመሰገንን ታስተምረኝ ዘንድ ወደኔ ና። እንዲህም እላለሁ፥

የዳዊት መዝሙር ገነትን ትመስላለች፣

በአበቦች አብባ ፍሬዎችን ታፈራለች፤

በረከትን ታመጣለች፤

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልአልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

አጋንንትን ታሳድዳለች፤

መላእክትንም ታቀርባለች ፤

ለዘለዓለሙ አሜን።

በሁሉም መዝሙራት መጀመሪያና መጨረሻ ላይ የሚባል ፦

ሰብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ።
(ምሥጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለዓለምና ለዘለዓለም ።)

የመጨረሻውን መዝሙረ ዳዊት (መዝ 150) እና (መዝ 140)ን የሚጸልየው ሰው የሚለው ጸሎት (ሙሉ ዳዊት የሚደገም ከሆነ ደግሞ በዓሥሩ የዳዊት መዝሙርና በዓሥራ አምስቱ ጸሎተ ነቢያት እንዲሁም በአምስቱ የሰሎሞን መኃልይ ጸሎት በኋላ የሚጸለይ ጸሎት) ፦

ሰብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ። ሰአሊ ለነ ቅድስት ማርያም ምሕረተ ወልድኪ የሐውጸነ እምእርያም ሰአል ለነ ዳዊት ቅድመ መንበሩ ለጸባዖት ኦ አምላከ ዳዊት አድኅነነ እምዕለት እኪት ወባልሐነ እምኩሉ መንሱት ። ለእለ ወለዱነ በሥጋ ወለእለ ሐጸኑነ በጸጋ ወለእለ መሀሩነ ቃለ ሃይማኖት ኅቡረ ይምሐሮሙ እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ፤ ወዕቀብ ሕይወተነ ወሥረይ ኃጢአተነ ወአድኅነነ እምዕለት እኪት ወእምሰዓታተ መንሱት ወእምኩሉ መቅሰፍት ለአግብርቲከ ወለአእማቲከ ---------- ለኩሎሙ ደቂቀ አንቀጸ ተዋሕዶ ።

ትርጉም ፦

ምሥጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለዓለምና ለዘለዓለም። እናታችን ቅድስት ድንግል ሆይ የልጅሽ ምሕረት ከአርያም ይጎበኘን ዘንድ ለምኚልን፤ (ነቢዩ) ዳዊት ሆይ በልዑሉ መንበር ፊት ለምንልን፤ የዳዊት አምላክ ሆይ ከዕለት መከራ ከዘመን መቅሰፍት አድነን/ሰውረን። በሥጋ የወለዱንንን፣ በጸጋ ያጸኑንን/ከፍ ከፍ ያደረጉንን፣ የሃይማኖት ቃል ያስተማሩንን ሁሉንም እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት ይማራቸው። አቤቱ ኃጢአታችንን ይቅር በለን፣ ሕይወታችንንም ጠብቅልን፣ ከዕለት መከራ፡ በየጊዜውም ከሚደርስ ችግር፡ ከዘመን መቅሰፍት አገልጋዮችህ የሆኑትን ----------እንዲሁም ሁሉንም የአንቀጸ ተዋሕዶ ልጆች ጠብቃቸው ለዘለዓለሙ አሜን።

ባዶ ቦታው ላይ መባዕ ያመጡትን ተማሪዎች ስመ ክርስትና አስገባ ።

ከይቄድሰዋ ቀጥሎ በጸሎት መሪው የሚደርሰ ጸሎት (ጸሎታ ለማርያም)

ጸሎታ ለማርያም ወሰአሊታ ያድኅነነ እምመዓት ወልዳ

0903111199 ፣ 0963132564
AnketseTewahido27@gmail.com
መልእልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

የማርያም ጸሎትና ምልጃ እኛን ከልጁ ቁጣ ይጠብቀን ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለፓትርያርክነ አባ ማትያስ ይዕቀቦ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ ፓትርያርካችን አባ ማትያስን ከልጁ ቁጣ ይጠብቃቸው ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለሊቀ ጳጳሰነ አባ ሄኖክ ይዕቀቦ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ ሊቀ ጳጳሳችን አባ ሔኖክን ከልጁ ቁጣ ይጠብቃቸው ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለኩሉሙ ኢጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ይዕቀቦሙ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ ኤጲስቆጶሳትን ቀሳውስትን እና ዲያቆናትን ከልጁ ቁጣ ይጠብቃቸው ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለመምህርነ አባ ገብረ ሥላሴ ይዕቀቦ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ መምህራችንን አባ ገብረ ሥላሴን ከልጁ ቁጣ ይጠብቃቸው ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለሕዝበ ክርሰቲያን ይዕቀቦሙ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ ሕዝበ ክርሰቲያንን ከልጁ ቁጣ ይጠብቃቸው ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለነፍሳተ መታን ያድኅኖ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ ነፍሳተ መታንን ከልጁ ቁጣ ያድናቸው ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለማኅበርነ አንቀጸ ተዋሕዶ ይዕቀባ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ አንድነታችንን አንቀጸ ተዋሕዶን ከልጁ ቁጣ ይጠብቃት ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለመካንነ መልዕልተ አድባራት ቀራንዮ ይዕቀባ እምመዓተ ወልዲ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ ቦታችንን መልዕልተ አድባራት ቀራንዮን ከልጇ ቁጣ ይጠብቃት ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ ይዕቀባ እምመዓተ ወልዳ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ አገራችንን ኢትዮጵያን ከልጇ ቁጣ ይጠብቃት ።

ጸሎታ ለማርያም ወሰእሊታ ለእግብርታ ወለእአማታ-------- ይዕቀቦሙ እምመዓተ ወልዳ

የማርያም ጸሎትና ምልጃ አገልጋዮቿን ------- ከልጇ ቁጣ ይጠብቃቸው ።

ትእዛዘ - በየጊዜው የሚሾሙ የሀገረ ሰብከቱ ፣ የደብሩ አባቶችን ሰም እየተካ ይጸልይ።

- ክፍት ቦታው ላይ መባዕ ያመጡ ሰዎችን ሰመ ክርስትና አሰገባ።

ክፍል ሁለት - ጸሎተ መሐረነ አብ - ኢትዮጵያ

✣ ሃሌ ሉያ ዘበእንቲአሃ ለቤተክርስቲያን ተጸፋእከ በውሰተ ዐውድ ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር።

- ሃሌ ሉያ ፤ ለቤተክርስቲያን ሰትል በአደባባይ በጥፊ የተመታህ አቤቱ ይህን ማድረግህ እርሰዋን በከበረ ደምህ ትቀድሳት ዘንድ ነው።

✣ ዘበእንቲአሃ ዝግሐታተ መዋቅሕት ፆረ። ወተዐገሠ ምራቀ ርኩሰ እንዘ አልቦ ዘአበሰ እምላክ ዲበ ዕፀ መሰቀል ተሰቅለ።

- ለእርሰዋ ሲል ታሰሮ መጎተትን የቻለ ፤ የበደለውን በደል ሳይኖር ርኩሰ ምራቅን ሲተፋበት የታገሰ አምላክ በእንጨት መሰቀል ላይ ተሰቀለ ።

✣ ሃሌ ሃሌ ሉያ እርእየነ እግዚኦ ሣህልከ ፤ ረዳኤ ኩነነ ወኢትግድፈነ፣ መሐረነ መሐከነ እግዚኦ እግዚኦ ተሣሃለነ።

- ሃሌ ሃሌ ሉያ አቤቱ ይቅርታህን አሳየን ፤ እርዳን አትተውን ፤ አቤቱ ማረን ይቅር በለን ።

በመሪ በተመሪ

መሐረነ አብ	ሃሌ ሉያ
- አብ ሆይ ማረን	- ሃሌ ሉያ

0903111199 ፣ 0963132564
AnketseTewahido27@gmail.com
መልአልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

ተሣሃለነ ወልድ - ወልድ ሆይ ይቅር በለን	**ሃሌ ሉያ** - ሃሌ ሉያ
መንፈሰ ቅዱሰ መሐሪ ተዘከረነ በሣህልከ (፫ ጊዜ) - ይቅር ባይ መንፈሰ ቅዱሰ ሆይ በይቅርታህ አሰበን	**ለከ ንፌኑ ሰብሐተ ወለከ ናዓርግ አኰቴተ።** - ለእንተ ፍጹም ምሰጋናን እናቀርባለን።
መሐረነ መሐሪ ኅጢአተነ አስተሥሪ። - ቸር ይቅር ባይ ሆይ ማረን ኃጢአታችንንም አስተሥርይልን	**ወእድኅነነ** - አድነን
ወተማኅፀን ነፍስነ ወሥጋነ - በነፍሰ በሥጋ ጠብቀን	**ክርስቶሰ ወልደ እግዚአብሔር** - የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ
እምላክነ - አምላካችን	**ወመድኃኒነ** - መድኃኒታችን
ኢየሱሰ ክርስቶሰ ተሣሃለነ - ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይቅር በለን።	**በብዝኀ ምሕረትከ** - በቸርነትህ ብዛት
ደምሰሰ እበሳነ - በደላችንን ደምስስ	**ወፈኑ ሣህለከ ላዕሌነ** - ይቅርታህንም ላክልን
እሰመ እምኀቤከ - ከአንተ ዘንድ	**ውእቱ ሣህል** - ይቅርታህን ላክልን።
ሃሌ ሉያ መሐረነ እብ መሐሪ - ሃሌ ሉያ ይቅር ባይ አብ ሆይ ማረን	**ወተሣሃለነ** - ይቅር በለን።
ሀብ ሣህለከ መሐሪ - መሐሪ የሆንህ አቤቱ ይቅርታን ስጠን፤	**ኢታጥፍአነ ተዘኪረከ ዘትካት** - የቀድሞ ኃጢአታችንን አስበህ አታጥፋን ።
በምሕረትከ - በቸርነትህ	**እሰመ መሐሪ እንተ** - እንተ ይቅር ባይ ነህና
ወብዙኅ ሣህልከ ለኩሎሙ እለ ይጼውዑከ - ለሚጠሩህ ለሚለምኑህ ሁሉ ይቅርታህ ብዙ ነው።	**ይጼውዑከ በጽድቅ** - በእውነት ይጠሩሃል

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልእልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

ሰማዒ ወትረ - አንተም ዘወትር ትሰማለህ	**ከሃሊ ዘውሰተ እድኅኖ** - ሁሉን ለማድረግ የምትችል ነህ።
ከሃሊ - የሚችል	**ዘውሰተ እድኅኖ** - ሁሉን ለማድረግ
ለእምላክነ አሰመ ጽድቅ ቃሉ። - የእምላካችን ቃሉ እውነት ነውና	**ንሰእሎ ለአብ** - አብን እንለምነው።
ይፈኑ ለነ ሣህሎ - ይቅርታውን ይልክልን ዘንድ	**እሰመ አብ የአክል ለዘሰአሎ** - አብ ለለመነው ሁሉ ይበቃልና።
ሃሌ ሉያ - ሃሌ ሉያ	**ሰብሑት ሎቱ ይደሉ** - ለእርሱ ምስጋና ይገባል።
ሃሌ ሉያ አኮቴት ሎቱ ይደሉ - ሃሌ ሉያ ለእርሱ ክብር ምስጋና ይገባል።	**ሃሌ ሉያ** - ሃሌ ሉያ
ለክርስቶስ ለእግዚአ ኩሉ - ሃሌ ሉያ ለሁሉ ጌታ ለክርስቶስ	**ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ** - ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ
ወይእዜኒ - ዛሬስ	**መኑ ተሰፋየ** - ተስፋዬ ማነው ?
እኮኑ	**እግዚአብሔር** - እግዚአብሔር አይደለምን ?
ውሰተ እዴከ እግዚኦ እመኀፅን ነፍሰየ - አቤቱ ነፍሴን ለእንተ አደራ አስጠብቃለሁ	**ኀበ እምላከ ምሕረት** - ከምሕረት ከቸርነት እምላክ ዘንድ
እመኀፅን ነፍሰየ። - ነፍሴን ለእንተ አደራ አስጠብቃለሁ	**ኀበ ንጉሠ ሰብሐት** - ከምሥጋና ንጉሥ ዘንድ
እመኀፅን ነፍሰየ። - ነፍሴን ለእንተ አደራ አስጠብቃለሁ	**በእግዚእየ ወእምላኪየ** - በጌታዬና በአምላኬ

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልአልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

እመጎፅን ነፍሰየ። - ነፍሴን ለእንተ እደራ አሰጠብቃለሁ	**እምኩሉ ምግባረ እኩይ አድኅና ለነፍሰየ (ፎጊዜ)** - ከክፉ ሥራ ነፍሴን (ሰውነቴን) አድናት
ሀቡ - ኑ	**ንሰእሎ** - እንለምነው
ንሰእሎ - እንለምነው	**ናስተምሕሮ** - እንማልደው
ለአምላክነ ጸድቅ እሰመ ጽድቅ ቃሉ - የእምላካችን ቃሉ እውነት ነውና።	**ዘይክል ኩሎ ወአልቦ ዘይሰዓኖ** - ሁሉን የሚችል የሚሳነው የሌለ እርሱ ነው
እምላከ ነዲያን ረዳኤ ምንዱባን - የድሆች እምላክ ለተቸገሩ ረዳት	**ንሕነ ኀቤከ ተማሳፀነ** - አቤቱ እኛ ወደ እንተ ተማፅነናል
ዘይክል ኩሎ ወአልቦ ዘይሰዓኖ - ሁሉን የሚችል የሚሳነው የሌለ እርሱ ነው	**እምላከ ነዲያን ናዛዜ ኅዘንን** - የድሆች አምላክ ተሰፋ ላጡ ተሰፋ የምትሆን
ንሕነ ኀቤከ ተማሳፀነ - አቤቱ እኛ ወደ እንተ ተማፅነናል	**ዘይክል ኩሎ ወአልቦ ዘይሰዓኖ** - ሁሉን የሚችል የሚሳነው የሌለ እርሱ ነው
እምላከ ነዲያን ወተሰፋ ቅቡፃን - የድሆች እምላክ ተሰፋ ላጡ ተሰፋ የምትሆን	**ንሕነ ኀቤከ ተማኀፀን** - አቤቱ እኛ ወደ እንተ ተማፅነናል
ዘነብረት : **- ኦ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ዓለም መሐረነ: ኦ ወልድ ዋሕድ ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ተሣሃለነ : ኦ ጰራቅሊጦሰ መንፈሰ ጽድቅ ሥረይ ለነ ሀሉ ምሰሌነ** (አቤቱ ዓለምን የያዝክ እግዚአብሔር አብ ሆይ ማረን፣ አቤቱ ወልድ ዋሕድ ኢየሱሰ ክርሰቶሰ ሆይ ይቅር በለን፣ አቤቱ የእውነት መንፈሰ ጰራቅሊጦሰ ሆይ በደላችንን ደምሰሰልን ከእኛ ጋር ሁን።) **- እሰመ እልብነ ረዳኢ በጊዜ ምንዳቤ ወኃዘን እሰመ ዘእንበሌከ ባዕድ እልቦ ዘእምር** (በችግራችንና በኀዘናችን ጊዜ የሚረዳን/የሚራዳን ከአንተ ውጪ የምናውቀው የለምና። (አብ ወልድ መንፈሰ ቅዱስ)	

0903111199 ፣ 0963132564
AnketseTewahido27@gmail.com
መልአልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

-ኤሎሄ ኤሎሄ ዘኢመ ትቤ በጽራሕከ ተማኅፀነ ምሕላነ ሰማዕ እምላክነ: (በመከራህ ሰዓት ኤሎሄ ኤሎሄ (አቤቱ አቤቱ) እንዳልክ አምላካችን ሆይ እኛም በእንተ ልመና ተማጽኖናልና ተለመነን ምሕላችንን ሰማ።) **- ነግህ ተዘከረነ ወነጽር ዲበ ቅኔነ ኖላዊነ ኄር ትጉህ ዘኢትነውም እንተ ሀሉ ምሰሌነ** (በጠዋት አሰበን ወደ ግዛታችንም ተመልከት፣ ቸሩ ጠባቂያችን/እረኛችን ትጉህ የማትተኛ እንተ ነህና ከኛ ጋር ሁን።	
ወበከመ ዐቀብከነ እምነግህ እስከ ሠርክ ዕቀበነ እግዚኦ እምሠርክ አስከ ነግህ /፫ጊዜ/ - ከጧት አስከ ማታ እንደ ጠበቅኸን አቤቱ እንዲሁ ከማታ እስከ ጧት ጠብቀን(ፎ)።	**ተሣሃልከ እግዚኦ ምድረከ ሃሌ ሉያ ሰማዕ ጸሎተነ ወሰእለተነ ወሥረይ ኩሎ ኃጢአተነ ሰማዕ ጸሎተነ ወሰእለተነ ዘሰማዕኮ ጸሎቶ ወሰእለቶ ለዕዝራ ተወከፍ ምሕላነ ሰላመከ ሀበነ እማዕከሌነ ኢትርኀቅ** - ሃሌ ሉያ አቤቱ ምድርህን ይቅር አልክ። ጸሎታችንን ልመናችንን ሰማ ። ኃጢአታችንን አቃልልን(ይቅር በል) የዕዝራን ጸሎትና ልመናን የሰማህ (አምላክ) የእኛንም ጸሎት ሰማ ምህላችን ተቀበል ፤ ሰላምህን ሰጠን ከመካከላችንም አትራቅ (ከእኛ አትለይ) ።
ወሚጥ መዓተከ እምኔነ ሃሌ ሉያ ንዒ ኀቤየ እንቲአየ ሠናይት ርግብየ መዓዛ አፉሃ ከመ ኮል ወኩሉ ነገራ በሰላም። ሃሌ ሉያ ቁጣህን ከእኛ መልሰ። መልካሟ ርግቤ የእኔ ሆይ ወደ እኔ ነዪ። የአፏ መዓዛ እንደ እንኮይ ነው። ነገሯም ሁሉ በሰላም ነው።	**እርእየነ እግዚእ ሣህለከ ሃሌ ሉያ መልእከ ሰላምነ ሊቀመላእክት ሚካኤል ሰአል ወጸሊ በእንቲኣነ እዕርግ ጸሎተነ ቅድመ መንበሩ ለንጉሥ ዐቢይ ።** - ሃሌ ሉያ አቤቱ ይቅርታህን አሳየን የሰላማችን መልአክ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ሆይ ሰለ እኛ ፈጽመህ ለምንልን። ከታላቁ ንጉሥ ከመንበሩ ፊት ጸሎታችንን አሳርግልን
ገብርኤል እብሠራ ለማርያም ወይቤላ ትወልዲ ወልደ፤ ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም፤ ወአልቦ ማኅለቅት ለሰላሙ። - ማርያምን ገብርኤል እበሠራት እንዲህም አላት። ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ ለያዕቆብ ቤት ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።	**ዮሐንስ ክቡር ነቢየ ልዑል ብእሴ ሰላም ዘኍብረቱ ገዳም።** - ክቡሩ የልዑል ነቢይ ፣ የሰላም ሰው ዮሐንስ መኖሪያው ገዳም ነው።
እመ ይትገበር ተዝካረ ትንሣኤየ ዘገሊላ ምሰለ እርዳእየ በህየ ንትራከብ ኩልነ እመ ይገብር በዓለ ይቤሎሙ ኢየሱስ ለእርዳኢሁ ማርቆስ ይበቁዓኒ ይሰብክ ትንሣኤየ በፍሥሐ ወበሰላም እክብርዎ ለማርቆስ	**ሰአል ለነ ጊዮርጊስ ጎበ እግዚአብሔር ወጸሊ በእንቲኣነ ሐረድዎ ወገመድዎ ወዘረዉ ሥጋሁ ከመ ሐመድ፣ ወወሰድዎ ጎበ ፷ ነገሥት ረገጸ ምድረ እንሥእ መታነ አባ ጊዮርጊስ በሰላም ዐደወ መንግሥተ ክብር ወረሰ።**

0903111199 ፣ 0963132564
AnketseTewahido27@gmail.com
መልአልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

- ከደቀ መዛሙርቴ ጋር የትንሣኤዬ መታሰቢያ በገሊላ ሲደረግ በዚያ እንገናኛለን። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ትንሣኤዬን ይሰብክ ዘንድ ማርቆስ ይበቃኛል ብሎ በዓልን ባደረገ ጊዜ አላቸዉ። ማርቆስንም በደስታና በሰላም አክብሩት ።	- ጊዮርጊስ ሆይ ወደ እግዚአብሔር ሰለእኛ ለምንልን። አርደው ከፋፈሉት ሥጋውንም እንደ ትቢያ በተኑት ወደ ፰ ነገሥታት ወሰዱት። ምድርን ረገጠ መታንን አስነሣ። አባ ጊዮርጊስ በሰላም (በጽናት) ተሸጋግሮ የክብርን መንግሥት ወረሰ ።
ባርከኒ አባ እንሣእ በረከተከ በእንተ ሰላማ ለቅድሰት ቤተ ክርስቲያን ሳሙኤል አባ ባርከኒ እንሣእ በረከተከ። - አባ በረከትህን እቀበል ዘንድ ባርከኝ ፤ ሰለ ቅድስት ቤተክርስቲያን ሰላም ሰትል በረከትህን እቀበል ዘንድ ባርከኝ።	**ጸድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ ወይበዝኅ ከመ ዘገባ ዘሊባኖሰ ገብረ መንፈሰ ቅዱሰ ኖመ ኖመ ኢየሩሳሌም በፍሥሐ ወበሰላም።** - ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፤ እንደ ሊባኖሰ ዝግባም ያድጋል። አባ ገብረ መንፈሰ ቅዱሰም በሰላምና በደስታ ኢየሩሳሌም ዐረፈ።
ብፁዕ አባ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘኤለ ገዳማተ እምጎበ እግዘኡ ይንሣእ ዕሴተ፤ ቦኡ ሀገረ ደብረ ሊባኖሰ በፍሥሐ ወበሰላም። - ከጌታው ዋጋን ይቀበል ዘንድ በበረሀ የተንገላታ አባታችን ተክለ ሃይማኖት ንዑድ ክቡር ነው። በሰላም በደስታ ወደ ደብረ ሊባኖሰ ገባ።	**ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሰዓማ እመ ተሰምዓ ዘናከ በዓለም ዘና ማርቆሰ ክቡር መምህረ ሰላም ዘህላዌከ ገዳም።** - ክቡር የሰላም መምህር አባ ዜና ማርቆሰ ሆይ ዜናህ በዓለም በተሰማ ጊዜ ምሕረትና ቅንነት ተገናኙ ጽድቅና ሰላምም ተሰማሙ።
ማኅደረ ሰላምነ ቅድሰት ደብተራ እሞሙ ለሰማዕት ወእኅቶሙ ለመላእክት ንዑ ንሰግድ ኩልነ ኅበ ማርያም እምነ። - የሰላም መገኛ ቅድሰት (የተከበረች ድንኳን) ቅድሰት ማርያም ናት። የሰማዕታት እናታቸው የመላእክት እኅታቸው ናት። ከእናታችን ማርያም ፊት ሁላችን እንሰግድ ዘንድ ኑ።	**መሰቀል ብርሃነ ለኩሉ ዓለም መሠረተ ቤተ ክርስቲያን ወህቤ ሰላም መድኃኔዓለም መሰቀል ለእለ ነአምን መድኅነ።** - ለዓለም ሁሉ መሰቀል ብርሃን ነው የቤተክርስቲያን መሠረት እርሱ ነው። ሰላምን የሚሰጥ ዓለምን የተቤዠህ (አምላክ) ሆይ ሰላምህን ሰጠን።
ሰላመ አብ ወሰላመ ወልድ ወሰላመ መንፈሰ ቅዱሰ የሀሉ ማዕከሌክሙ አኀው። /፫ ጊዜ በመሪና በተመሪ/ - የአብ ሰላም የወልድ ሰላም የመንፈሰ ቅዱሰ ሰላም ወገኖች (ወንድሞች) ሆይ ከእናንተ ጋር ይሁን። **እግዚኦ መሐረነ ክርስቶሰ /፫ ጊዜ በመሪና በተመሪ/** - አቤቱ ክርስቶሰ ሆይ ይቅር በለን ።	
ሰብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ - እናመልከው ዘንድ ለፈጠረን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባል።	**ሰብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ** - እመቤታችንና መድኀኒታችን ለኾነች ለአምላክ እናት ለማርያም ምስጋና ይገባል።
ሰብሐት ለመሰቀለ ክርስቶሰ ዕፀ መድኃኒት ኃይልነ ወፀወንነ - ኃይላችን፣ መጠጊያችን ለኾነ፣ ድኅነት ለተገኘበት ለክርስቶሰ መሰቀል ምስጋና ይገባል ።	

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልእልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

ጸሎተ ሃይማኖት ይደገማል።

የክርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወናል? ጎዘነ ነውን? መከራ ነውን ? መሰደድ ነውን ? መራብ ነውን ? ጭንቀት ነውን ? ሾተል ነውን ? ሰለእንተ ዘወትር ይገድሉናል እንደሚታረዱ በጎች ሆንን ብሎ መጽሐፍ እንደተናገረ ፤ ነገር ግን እሱ ወዶናልና ሁሉን ድል እንነሳዋለን። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዲሆን አምናለሁ ሞትም ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም አለቆችም ኃይላትም ያለውም የሚመጣውም ወደ ላይ ቢያወጡን ወደ ገደልም ቢጥሉን ሌላም ፍጥረትም ቢሆን የክርስቶስን ፍቅር ሊያስተወን የሚችል የለም(ሮሜ 8 ፥ 35)

ኢትዮጵያ ሆይ ሀገራችን ረስቼሽ እንደኾን ቀኜ ትርሳኝ

ያላሰብኩሽ እንደሆን አንደበቴ ከጉሮሮዬ ይጣጋ

ኢትዮጵያ ሆይ ለቀድሞ ክብርሽ ያልተሳልኩ እንደኾን

አቤቱ ፈጣሪያችን የጠላት ልጆች

ኢትዮጵያን ያጠፉበትን ቀን አሰብ

እሰከ መጨረሻው ትጥፋ ያሉትን

ጠላቶቻችንን የሚያጠፋቸው አምላካችን ምሰጉን ነው

ጠላቶችሽን በጽኑዕ መከራ

የሚያጠፋቸው አምላካችን ምሰጉን ነው

ኢትዮጵያ ሆይ ሀገራችን ረስቼሽ እንደኾን ቀኜ ትርሳኝ

እጅሽን ዘርግተሽ የለመንሽባት ምድር

ተንኮለኛ ያዙት ኑፋቄ ጥርጥር

ኢትዮጵያ እናታችን እያልን ሰናለቅሰ

በመከራችን ቀን ዕንባችን ይታበስ

ኢትዮጵያ ሆይ ሀገራችን ረስቼሽ እንደኾን ቀኜ ትርሳኝ

መግለጫ - የቤተክርስቲያን የጸሎት መጽሐፍ ከሚለው የተወሰደ ፤ ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ኃይለ ሥላሴም እንግሊዝ አገር በነበሩ ሰዓት በንጉሡ ትእዛዝ የተዘጋጀ መዝሙራዊ ጸሎት

0903111199 ፣ 0963132564
AnketseTewahido27@gmail.com
መልእልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

ክፍል ሦስት - ጸሎተ ቅዱስ ወንጌል

ይ.ዲ. - ተንሥኡ ለጸሎት (ለጸሎት ተነሡ)

ይ.ሕ. - እግዚኡ ተሣሃለነ (አቤቱ ይቅር በለን)

ይ.ካ. - ሰላም ለኩልክሙ (ሰላም ለሁላችሁም)

ይ.ሕ. - ምስለ መንፈስከ (ከመንፈስህ ጋራ)

ሐተታ ፦ ተንሥኡ ለጸሎትን ማን ተናግሮታል? ቢሉ አዳም በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ለዕለት እትወሊድ እምወለተ ወለትከ ያለውን ይዞ በሲኦል ሲቄጥር ኑሯል ጌታ በዕለተ ዓርብ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ አባ አመሐፅን ነፍሰየ ውስተ እዴከ ባለ ጊዜ የተነገረው ትንቢት የተቈጠረው ሱባዔ ደረሰ እድንሃለሁ ብሎኛ ነበረ ቀረን ይሆን እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ተንሥኡ ለጸሎት አላቸው ነፍሳትም እግዚኡ ተሠሃለነ ብለዋል ጌታ ወዳያው በአካለ ነፍስ ወርዶ ሰላም ለኩልክም ብሎ በሲኦል ብርሃነ መለኮቱን ነዛባት። ነፍሳትም ምስለ መንፈስከ (እንደ ቸርነትህ እንደ ይቅርታህ ይደረግልን ማለት ነው።)ብለው ወጥተዋል መልኩን ማየትም ልጅነት ሁኑዋቸዋል ቢሉ የማነ እዴየ መጠውክዋሙ ወኮነቶሙ ጥምቀተ ይላል ቀኝ እጁን ሰጥቷቸው ቢሉ በዚያም በዚያም ልጅነትን አግኝተው ወጥተዋል። **ምንጭ ፦ የ14ቱ ቅዳሴያት ትርጓሜ**

ይ.ካ - እግዚኡብሔር እግዚኡ ኢየሱስ ክርስቶስ እምላክነ ዘቡቤሎሙ ለእርዳኢከ ቅዱሳን ወለሐዋርያቲከ ንጹሐን እሰመ ብዙኃን ነቢያት ወጻድቃን ፈተዉ ይርእዩ እንትሙ ዘትሬእዩ ወኢርእዩ ወፈተዉ ይሰምዑ እንትሙ ዘትሰምዑ ወኢሰምዑ። ወለክሙሰ ብፁዓት እዕይንቲክሙ እለ ርእያ ወእእዝኪክሙ እለሰምዓ። ወከማሆሙ ለነኒ ረሰየነ ድልዋነ ንሰማዕ ወንግበር ቃለ ወንጌልከ ቅዱሰ በጸሎቶሙ ለቅዱሳን ።

(አቤቱ አምላካችን እግዚኡብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ቅዱሳን የሚሆኑ ደቀ መዛሙርትህንና ንጹሐን ሐዋርያትን እንዲህ ያልሃቸው እናንተ የምታዩትን ያዩ ዘንድ ብዙ ነቢያት ጻድቃን ወደዱ አላዩም፣ እናንተ ዛሬ የምትሰሙትንም ይሰሙ ዘንድ ወደዱ አልሰሙም፣ የእናንተ ያዩ ዓይኖቻችሁና የሰሙ ጆሮቻችሁ ግን የተመሰገኑ ናቸው። እኛንም እንደነሱ አድርገን፣ በቅዱሳን ጸሎት የከበረ የወንጌልን ቃል ሰምተን እንሠራ ዘንድ ።)

ይ.ዲ. ጸልዩ በእንተ ወንጌል ቅዱሰ (ክቡር ሰለሚሆን ሰለ ወንጌል ጸልዩ)

ይ.ሕ. ረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዐ ወንጌል ቅዱሰ (የከበረ ወንጌልን ለመሰማት የበቃን ያድርገን)

ይ.ዲ. ምሰባክ ፦ ከመዝሙረ ዳዊት ለዕለቱ የሚሰማማውን (መጽሐፈ ግጻዌ የሚያዘውን) ይበል

ለአብነት ፦ እግዚኡብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም

ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር

እንተ አጽናዕካ ለባሕር በኃይልከ። መዝ (73 ፥ 12)

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልእልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08

ትርጉም ፦

እግዚአብሔርሰ ከዓለም እሰቀድሞ ንጉሥ ነው ፣

በምድር መካከል መድኃኒትን እደረገ ።

እንተ በኃይልህ ባሕርን እጸናኻት። ሕዝቡ ከዲያቆኑ ቀጥለው 3 ጊዜ ይበሉ።

ምስባክ 5 ጊዜ መባሉ 5500 ዘመን ሰለ ክርስቶስ መምጣት ትንቢት የመነገሩ ምሳሌ ነው። **ምንጭ ፦ የ14ቱ ቅዳሴያት ትርጓሜ**

ይ.ዲ. ሃሌ ሉያ ቁሙ ወእጽምዑ ወንጌለ ቅዱስ ዜናሁ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱሰ ክርስቶሰ። (ሃሌ ሉያ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ወንጌልን ቆማችሁ ሰሙ።)

ይ.ካ.እግዚአብሔር ምሰለ ኩልክሙ (እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋር ይሁን)

ይ.ሕ. ምሰለ መንፈስከ (ከመንፈስህ ጋራ)

ይ.ካ- ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ——(ማቴዎሰ፣ ማርቆሰ፣ ሉቃስ)(ዘሰበኩ ዮሐንሰ) ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

በማቴዎሰ ወበማርቆሰ ወበሉቃሰ ዘዜነወ ይበል። በዮሐንሰ ዘሰበከ ይበል።

ዮሐንስ የሰበከው የእግዚአብሔር ልጅ ቃል ቅዱስ ወንጌል ይህ ነው።በማቴዎስና በማርቆስ በሉቃስም የተናገረው ይበል ።

ይ.ሕ ፦ ሰብሐት ለከ ክርስቶሰ እግዚእየ ወእምላኪየ ኩሎ ጊዜ

(ጌታዬና አምላኬ ክርስቶስ ሆይ ሁልጊዜ ላንተ ምስጋና ይገባል)

ይ.ካ ፦ ነዋ ወንጌለ መንግሥቱ ለወልደ እግዚአብሔር (ወደ መንግሥተ ሰማያት የምታገባ ወንጌል እነሆ)

ይ.ካ ፦ (ንፍቅ) : መንግሥቶ ወጽድቆ ዘኢወፈየኒ እወፈይኩከ (መንግሥቱንና ጽድቁን እንደሰጠኸኝ ሰጠሁህ)

ይ.ዲ ፦ ነሰሉ እሰመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት (መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሰሐ ግቡ)

ይ.ካ፡ እንዘ ያነብብ - ባርክ እግዚኦ ዘእምወንጌለ እገሌ ረድኡ ወሐዋርያሁ ለእግዚእነ ኢየሱሰ ክርስቶሰ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው ሎቱ ሰብሐት ወትረ እሰከ ለዓለመ ዓለም አሜን።

በማቴዎሰ ወበማርቆሰ ወበሉቃሰ ከመዝ ይበል በበሰሞሙ ለፒቲሆሙ። ዮበስ ወንጌለ ዮሐንሰ ይበል : ዝ ቃል ዘኢግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱሰ ክርስቶሰ ለክብረ መንግሥቱ ሰብሐት እሰከ ለዓለም።

ወንጌልን ሲያነብ ፦የሕያው እግዚአብሔር ልጅ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያውና ደቀመዝሙሩ ከሚሆን ከእገሌ ወንጌል የተገኘውን ቃል አቤቱ ባርክ ምስጋና ዘወትር ገንዘቡ ነው ለዘላለሙ አሜን ።

በማቴዎስና በማርቆስ በሉቃስም በሦስቱ በየስማቸው እንዲህ ይበል። የዮሐንስን ወንጌል ሲያነብ ግን እንዲህ ይበል ። ለመንግሥቱ እስከ ዘላለም ምስጋና ይግባውና ይህ ቃል የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

<u>በጸሎትና በቅዳሴ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃላት ሲነበቡ የሰማያዊውን ንጉሥ የተከበረ የወንጌሉን ቃል ለመስማት ከመጀመሪያቸው እስከ መጨረሻቸው ድረስ ከማመስገንና ከመቀደስ በቀር ማድነቅና ጸጥታሊሆን ይገባል ። የምድራዊ ንጉሥ ደብዳቤ ሲነበብ እንድ ሰው እንኳ ለመናገር የማይደፍር ከሆነ ቢናገርም ግርፋትና ቅጣት የሚያገኘው ከሆነ የሰማያዊ ንጉሥ ደብዳቤ የሚሆን ወንጌል ሲነበብማ ቢናገር እንደምን እንደርሱ ያገኘው ይሆን ። ምንጭ ፦ መጽሐፈ ቅዳሴ</u>

ቅዱስ ወንጌል ከተነበበ በኋላ

በማቴዎስ ወንጌል ፦ ይ.ካ ሰማይ ወምድር የኀልፍ ወቃልየስ ኢየኀልፍ ይቤ እግዚእ ለአርዳኢሁ ።

(ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም አለ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ።)

በማርቆስ ወንጌል ፦ይ.ካ ዘቦ ዕዝን ሰሚዐ ለይሰማዕ ።

(ጆሮ ያለው መሰማትን ይሰማ ።)

በሉቃስ ወንጌል ፦ይ.ካ ይቀልል ኅልፈተ ሰማይ ወምድር እምትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት ወእምነቢያት ።

(ከኦሪትና ከነቢያት አንዲቱ ቃል ከምትወድቅ የሰማይና የምድር ማለፍ ይቀላል አለ ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ።)

በዮሐንስ ወንጌል ፦ይ.ካ ዘየእምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ።

(በወልድ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት አለው።)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ወለወላዲቱ ድንግል

ወለመስቀሉ ክቡር አሜን።

0903111199 ፣ 0963132564

AnketseTewahido27@gmail.com

መልአልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኀኔዓለም እና ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን፤
ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08